**የአሜሪካ ነፍስ-አድን እቅድ ለዲስትሪክት ኗሪዎች የጤና መድን ፕሪሚየሞችን ይቀንሳል**

የ2021 የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ሕግ (የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ) የጤና መድን ፕሪሚየሞችን ይቀንሳል። ለDC ነዋሪዎች፣ የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ በ DC Health Link በኩል ለጤና መድን ፕሪሚየሞችን ይቀንሳል፣ ስራቸውን ላጡ ሰዎች እስከ $2/ወር ለሚያንስ ዋጋ የጤና መድን ያቀርባል፣ እና 100% የኮብራ (COBRA) ፕሪሚየም ሥራ-ላቆሙ ሰራተኞች ተከፍሏል።

# በ2021 እና 2022 ወርሃዊ የፕሪሚየም ቅናሾች ለDC HEALTH LINK ደንበኞች

**የግል የጤና መድን ማግኘት እንድችል የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ እንዴት ይረዳኛል?**

የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ በDC Health Link ላይ የጤና መድን ፕሪሚየሞችን ይቀንሳል።

**እኔ ቀድሞውኑ የፕሪሚየም ቅናሾችን አገኝቻለሁ። የእኔ ፕሪሚየሞች ይቀንሳሉ?**

**አዎ።** የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ የእርስዎ ፕሪሚየሞችን ይቀንሳል። ለምሳሌ፣ እርስዎ የ30-ዓመት-እድሜ ባለቤት ሆነው የ $30,000 ዓመታዊ ገቢ ያለዎት እና ቀድሞውኑ የ $200/ወር ቅናሽ ፕሪሚየምን ለሲልቨር እቅድ የሚከፍሉ ከሆነ፣ የእርስዎ ወርሃዊ ፕሪሚየም ወደ $90/ወር ይወርዳል።

**እኔ በተመጣጣኝ እንክብካቤ ሕግ (ACA) ስር ለቅናሽ ፕሪሚየሞች ብቁ አልሆንም። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ የእኔን ፕሪሚየሞችን ይቀንሳል?**

**አዎ።** የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ እርስዎ የገቢዎ 8.5% በላይ ፕሪሚየሞች ላይ እንዳይከፍሉ የእርስዎን ፕሪሚየሞችን ይቀንሳል። ለምሳሌ፣ እርስዎ የ30-ዓመት-እድሜ ነዋሪ ሆነው የ $45,000 ዓመታዊ ገቢ ያለዎት እና ቀድሞውኑ የ $377/ወር ሙሉ ፕሪሚየምን ለሲልቨር እቅድ የሚከፍሉ ከሆነ፣ የእርስዎ ወርሃዊ ፕሪሚየም ወደ $282/ወር ይወርዳል።

ACA ገቢዮቻቸው እስከ 400% የፌዴራል ደህነት ደረጃ (FPL) -- $51,040 በዓመት (ወይም $104,800 በዓመት 4 አባል ላለው ቤተሰብ) ለሆነ ሰዎች ፕሪሚየሞችን ቀንሷል። ከፍተኛ ገቢ አለዎት ማለት እርስዎ በACA ስር ለፕሪሚየም ቅናሾች ብቁ አይሆኑም ማለት ነው። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ሁሉንም ሰዎች ይጠብቃል። ማንም ሰው የጤና መድን ፕሪሚየሞች ላይ የገቢውን 8.5% በላይ አይከፍልም።

**እኔ በቪሳ U.S. ውስጥ እገኛለሁ እና በቪዛየ ሁኔታ ምክኒያት ለMedicaid ሽፋን ብቁ አልሆንም። ለግል ጤና መድን የእኔ ፕሪሚየሞች ይቀንሳሉ?**

**አዎ።** በገቢዎ መሠረት፣ የእርስዎ ፕሪሚየሞች እስከ $2/ወር ሊወርዱ ይችላሉ። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ለMedicaid ሽፋን ብቁ የማይሆኑ ስድተኞችን ያካትታል። ለተነሱ ፕሪሚየሞች ብቁ የሆኑ የስድተኞች ምድቦችን ለማግኘት ብቁ የሆኑ የኢሚግሬሽን ሁኔታ (ስታተስ) ለግል የጤና ሽፋን በDC Health Link አማካኝነት FAQ (በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች) ገጽን ይጎብኙ።

**እኔ ብመዘገብ፣ የእኔ ፕሪሚየሞች ለምን ያህል ጊዜ እንዲህ ወርዶ ይቆያል?**

የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ስር ያለው የተቀነሰ ፕሪሚየም ለሙሉ 2021 እና 2022 ይቆያል፣ ኮንግሬስ ካራዘመው ወይም ዘላቂ ካላደረገው በስተቀር።

**የእኔ ገቢ ቢለወጥስ?**

የእርስዎ ወርሃዊ ፕሪሚየም በገቢዎ ላይ የተመሠረተ ነው። የእርስዎ ገቢ ከወረደ፣ ለሚቀንሱ ወርሃዊ ፕሪሚየሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የእርስዎ ገቢ ከጨመረ፣ የእርስዎ ወርሃዊ ፕሪሚየም ሊጨምር ይችላል። እርስዎ የጤና መድን ፕሪሚየሞች ላይ የገቢዎን 8.5% በላይ አይከፍልም።

**ልዩ እቅድ ውስጥ መመዝገብ ይኖርብኛል?**

**አይ።** እርስዎ በማንኛውም እቅድ – ብሮንዝ (ናስ)፣ ሲልቨር (የብር)፣ ጎልድ (የወርቅ)፣ ወይም ፕላቲነም – ውስጥ መመዝገብ እና ለመረጡት እቅድ ብቁ ለሚሆኑለት የወርሃዊ ቅናሾች መጠን ማመልከት ይችላሉ። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ የሁለተኛ ዝቅተኛ የሆነ የሲልቨር እቅድ ዋጋን፣ ገቢዎን፣ እና እድሜዎን በመጠቀም የእርስዎን ወርሃዊ የፕሪሚየም ቅናሾችን ለመወሰን የቅናሽ መጠንን ያሰላል።

**የሁሉም ሰዎች ፕሪሚየም ይቀንሳል?**

**አይ።** ተመጣጣኝነቱ የሁለተኛ ዝቅተኛ በሆነ የሲልቨር እቅድ ዋጋ፣ ገቢ፣ እና እድሜ ስለሚወሰን ለወርሃዊ የፕሪሚየም ቅናሾች ብቁ የሚሆኑት ሁሉም ሰዎች አይደሉም። የDC ፕሪሚየሞች ቀድሞውኑ በሀገሪቷ ውስጥ ካሉት የተወሰኑ በጣም ዝቅተኛ ከሚባሉት ውስጥ ስለሆኑ፣ የተወሰኑ ሰዎች ቀድሞውኑ የገቢያቸውን 8.5% ፕሪሚየሞች ላይ ይከፍላሉ።

**እኔ ለወርሃዊ የፕሪሚየም ቅናሾች ብቁ እሆናለሁ፣ ግን የእርሱን ፋንታ የእኔን ሙሉ ወርሃዊ ፕሪሚየም ለመክፈል እመርጣለሁ። የተቀነሱ የፕሪሚየሞች መጠንን በግብር ጊዜ ወቅት ግብሬን ሳስገባ መጠየቅ እችላለሁ?**

**አዎ።** ግብሮችዎን ሲያስገቡ የተቀነሱ የፕሪሚየሞች መጠንን ማግኘት ይችላሉ። ያንን ሲያደርጉ፣ በየወሩ ሙሉ ክፍያን ለፕሪሚየሞች ይከፍላሉ።

**ይህ አዲስ ጥቅማጥቅም መቼ የDC Health Link ላይ ይወጣል?**

ይህ አዲስ ጥቅማጥቅም ከአፕሪል ጀምሮ DCHealthLink.com ላይ ይወጣል።

**እኔ ባሁን ጊዜ በDC Health Link በኩል የጤና እቅድ ውስጥ ተመዝግቤያለሁ እና ለፕሪሚየሞች ሙሉ ክፍያን እከፍላለሁ። ዝቅተኛ ወርሃዊ ፕሪሚየሞችን ለማግኘት ምን ማድረግ ይኖርብኛል?**

ከአፕሪል ጀምሮ፣ በ DCHealthLink.com አካውንትዎ በኩል የገቢ እና የቤተሰብ መረጃን ማቅረብ ይችላሉ እና የሚቀንስ ከሆነና ወርሃዊ ፕሪሚየሞችዎ በምን መጠን እንደሚቀንሱ ወዲያውኑ ያውቃሉ። እንዲሁም እነዚያን ፕሪሚየም ቅናሾችን መተግበር እና አዲሱን ፕሪሚየምዎን ማየት ይችላሉ።

**እኔ ባሁን ጊዜ DC Health Link ላይ ተመዝግቤያለሁ እና የተቀነሱ ወርሃዊ ፕሪሚየሞችን እየከፈልኩ ነው። የእኔ ወርሃዊ ፕሪሚየሞችን የበለጠ ለመቀነስ ምን ማድረግ ይኖርብኛል?**

ምንም። አፕሪል ውስጥ፣ DC Health Link ባሁን ጊዜ ACA ስር ወርሃዊ የፕሪሚየም ቅናሾችን ለሚወስዱ ደንበኞች ብቁነትን ወዲያውኑ ደግሞ ያሰላል። ቀድሞውኑ ባቀረቡት መረጃ መሠረት፣ ወዲያውኑ ዝቅተኛ ወርሃዊ ፕሪሚየሞችን ይመለከታሉ። ይህም ከጤና መድን ኩባኒያዎ የሚላከው የእርስዎ የሜይ የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝ ላይ ይገለጻል። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ እነዚህን ለውጦች ከጃንዋሪ 1, 2021 ጀምሮ ስራ ላይ ስለሚያውል፣ ከጃንዋሪ 2021 ጀምሮ ከተሸፈነልዎ የፕሪሚየሙን ሙሉ ዋጋ ይቀበላሉ።

ለምሳሌ፣ ለ $100/ወር ቅናሽ (ወይም $1,200/ዓመት ቅናሽ) ብቁ ከሆኑ እና ከጃንዋሪ 1, 2021 እስከ ዲሴምበር 31, 2021 ከተመዘገቡ፣ ከሜይ እስከ ዲሴምበር ያሉ የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኞች በየወሩ የ $150 (የ$1,200/ዓመት ሙሉ ቅናሽ) የፕሪሚየም ቅናሽን ይገልጻሉ። አዲሱን ቁጠባን ላሁኑ የማያሳይ የሜይ የመጀመሪያ የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝን መቀበል እንደሚችሉ ያስታውሱ። የተሻሻሉ የፕሪሚየም ቅናሾችን ለሚያሳይ የሜይ ፕሪሚየም፣ የጤና እቅዱ የተሻሻለውን የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝ በአፕሪል መጨረሻዎች ይልካል።

**እኔ ባሁን ጊዜ DC Health Link ላይ አልተመዘገብኩም። በአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ የሚቀርቡ ዝቅተኛ ወርሃዊ ፕሪሚየሞችን ለማግኘት ምን አደርጋለሁ?**

አፕሪል ውስጥ በመጀመር፣ ወደ [DCHealthLink.com](DCHealthLink.com) መሄድ እና የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ስር ለምን ያህል የፕሪሚየም ቅናሾች ብቁ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማየት ፈጣን ምልከታ ማድረግ ይችላሉ። ስለ ገቢዎ እና ቤተሰብዎ መረጃ ያቅርቡ፣ ፕሪሚየሞችዎ በምን ያህል እንደሚቀንሱ ይወቁ፣ የጤና እቅድ ይምረጡ፣ እና ይመዝገቡ።

**የአሜሪካ ነፍስ አድን እቅድ ክፍት ምዝገባ እና የCOVID-19 ልዩ የምዝገባ ጊዜ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

ሁለቱም የአሜሪካ ነፍስ አድን እቅድ ክፍት ምዝገባ እና የCOVID-19 ልዩ የምዝገባ ጊዜ የDC ኗሪዎች የግል የጤና ሽፋን ውስጥ እንዲመዘገቡ እድል ይሰጧቸዋል። ሁለቱ መካከል ያለው ብቸኛው ልዩነት ሽፋንዎ መቼ እንደሚጀምር ላይ ነው።

**የአሜሪካ ነፍስ አድን እቅድ ክፍት ምዝገባ ስር፣** እቅድዎ የሚጀምረው መቼ እንደሚመዘገቡ ላይ ተመስርቶ ነው፥

| **የምዝገባ ቀን፥** | **የሽፋን መጀመር፥** |
|---|---|
| አፕሪል 1 – አፕሪል 15 | ሜይ 1 |
| አፕሪል 16 – ሜይ 15 | ጁን 1 |
| ሜይ 16 – ጁን 15 | ጁላይ 1 |

**የCOVID-19 ልዩ የምዝገባ ጊዜ ስር፣** ሽፋንዎ በተመዘገቡበት ወር ወይም የሚቀጥለው ወር መጀመሪያ ላይ እንዲጀምር መምረጥ ይችላሉ።

**ለምሳሌ፥** በአፕሪል 21 ከተመዘገቡ፣ ሽፋን በአፕሪል 1 ወይም ሜይ 1 እንዲጀምር መምረጥ ይችላሉ።

# የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ለዲስትሪክት ነዋሪዎች ወርሃዊ ፕሪሚየሞችን እንዴት እንደሚቀንስ ምሳሌዎች

የ 2021 በ DC Health Link ላይ ሁለተኛ ዝቅተኛ ወጪ ሲልቨር እቅድ ላይ የተመሰረቱ ምሳሌዎች።

## ወርሃዊ ፕሪሚየሞች 30-ዓመት እድሜ-ላለው

| **ዓመታዊ ገቢ** | **ACA** | **የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ** |
|---|---|---|
| $30,000.00 | $200.07 | $90.43 |

| ዓመታዊ ገቢ | ACA | የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ |
|---|---|---|
| $45,000.00 | $332.51 | $279.70 |
| $60,000.00 | $332.51 | $332.51[1] |

### ወርሃዊ ፕሪሚየሞች 45-ዓመት እድሜ-ላለው

| ዓመታዊ ገቢ | ACA | የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ |
|---|---|---|
| $30,000.00 | $202.82 | $93.18 |
| $45,000.00 | $376.70 | $282.44 |
| $60,000.00 | $504.09 | $433.07 |

### ወርሃዊ ፕሪሚየሞች 60-ዓመት እድሜ-ላለው

| ዓመታዊ ገቢ | ACA | የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ |
|---|---|---|
| $30,000.00 | $209.08 | $99.44 |
| $45,000.00 | $382.96 | $288.70 |
| $60,000.00 | $895.93 | $439.34 |

[1] የፕሪሚየም ቅናሽ የለውም ምክኒያቱም የሽፋን ወጪ የገቢ ተመጣጣኝነት ጥበቃ 8.5% በታች ስለሆነ።

## በ 2021 ውስጥ የስራ-አጥነት ካሳ ለተቀበሉ የዲስትሪክት ነዋሪዎች እስከ $2/በወር ድረስ ለሚወርድ ዋጋ በ DC Health Link በኩል ለግል ጤና መድን ብቁ መሆን

**ክሥራ-ከተገለልኩኝ የግል የጤና መድን ማግኘት እንድችል የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ እንዴት ይረዳኛል?**

የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ DC Health Link ላይ የጤና መድንን ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ደረጃ ነፃ ያደርጋል። በመረጡት የእቅድ ዓይነት ላይ በመመስረት እስከ $2/ወር ድረስ የሚችለውን ይክፈሉ።

**በ2021 ውስጥ የሥራ-አጥነት ካሳ ከተቀበልኩኝ ብቁ እሆናለሁ?**

**አዎ።** በ2021 ውስጥ በማንኛውም ጊዜ የሥራ-አጥነት ካሳ ከተቀበሉ ብቁ ይሆናሉ። ለጤና መድን ሲያመለክቱ የሥራ-አጥነት ካሳ እየተቀበሉ መሆን አይኖርብዎትም።

ለምሳሌ፣ ከጃንዋሪ 1 እስከ ጃንዋሪ 7, 2021 ድረስ የሥራ-አጥነት መድን ተቀብለው ከሆነ እና በኤፕሪል 1, 2021 ለጤና መድን አመልክተው ከሆነ፣ ለ $2/ወር ለጤና መድን ብቁ ይሆናሉ ምክኒያቱም በ 2021 ውስጥ ቢያንስ ለአንድ ሳምንት የሥራ-አጥነት መድን ተቀብለዋል።

**እንደ Medicaid፣ Medicare፣ ወይም በአሠሪ-ስፖንሰር የተደረገ ሽፋን ላሉ ሌሎች ሽፋን ብቁ ከሆንኩኝ ብቁ እሆናለሁ?**

**አይ።** እንደ Medicaid፣ Medicare፣ ወይም በአሠሪ-ስፖንሰር የተደረገ ሽፋን ላሉ ሌሎች ሽፋን ብቁ ከሆኑ፣ ብቁ አይሆኑም።

**ምን ዓይነት የሥራ-አጥነት ካሳ ነው ብቁ የሚያደርገው?**

ሁሉም የሥራ-አጥነት ካሳ ዓይነቶች ብቁ ያደርጋሉ። ይህ የሚጨምረው መደበኛ የሥራ-አጥነት ካሳ፣ የወረርሽኝ የአስቸኳይ አዋጅ ጊዜ የሥራ-አጥነት ካሳ (PEUC)፣ የተራዘመ የሥራ-አጥነት ካሳ፣ እና የወረርሽኝ የሥራ-አጥነት እርዳታ (PUA)።

**አንዴ ከተመዘገብኩኝ የእኔ ፕሪሚየሞች ለምን ያህል ጊዜ ዝቅተኛ ሆነው ይቆያሉ?**

ይህ ጥቅማጥቅም ባሁን ጊዜ ጊዜያዊ ጥቅማጥቅም ነው እና ኮንግሬስ ካላራዘመው ወይም ዘላቂ ካላደረገው በስተቀር በዲሴምበር 31, 2021 ጊዜው ያበቃል።

**እኔ የጤና እቅዴን ሲጠቀም በተጨማሪ ለዝቅተኛ ተቀናሾች፣ የጋራ ክፍያዎች፣ እና የጋራ መድን ብቁ እሆናለሁ?**

**አዎ።** እርስዎ በተጨማሪም የወጪ-መጋራት ቅናሾችን ያገኛሉ፣ ግን የሲልቨር ደረጃ እቅድን መምረጥ አለብዎት። በየተኛውም የሲልቨር እቅድ ውስጥ ሲመዘገቡ፣ እርስዎ ዓመታዊ ተቀናሾችን አያገኙም እና ጥቅማጥቅሞችዎን ሲጠቀሙ በጣም ዝቅተኛ የጋራ ክፍያዎች እና የጋራ መድኖችን ያገኛሉ። እርስዎ በፕላቲነም፣ ጎልድ፣ ወይም ብሮንዝ እቅድ ውስጥ ከተመዘገቡ፣ መደበኛ ተቀናሾቹ፣ የጋራ-ክፍያዎቹ፣ እና የጋራ-መድኖቹ ይተገበራሉ።

**የ DC Health Link መቼ ነው ይህን አዲስ ጥቅማጥቅም የሚኖረው?**

ይህ አዲስ ጥቅማጥቅም ከኤፕሪል ጀምሮ DC Health Link ላይ ይወጣል። ለመመዝገብ ወደ DCHealthLink.com ይሂዱ።

# ነፃ ኮብራ ከሥራ-ለተነሱ ነዋሪዎች

**እኔ ከሥራ-ተነስቻለሁ። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ለኮብራ (COBRA) ፕሪሚየሞቼ እንድከፍል እንዴት ይረዳኛል?**

የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ለእርስዎ COBRA ፕሪሚየሞች **100%** ይከፍላል። ለበለጠ ዝርዝር ወደ፥ https://www.dol.gov/agencies/ebsa/laws-and-regulations/laws/cobra/premiu... ይሂዱ።

**ኮብራ(COBRA) ምንድን ነው?**

COBRA ከ 20 ወይም ከዚያ በላይ ሠራተኞች ባላቸው አሰሪዎች የሚቀርብ የቀጣይነት የጤና መድን ሽፋን ነው። የፌዴራል ሕግ አሰሪዎች ይህን ጥቅማጥቅም እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። እርሱ ከስራ-ለተቀነሱ ሠራተኞች ለ 18 ወራት ይቆያል። ከ 20 በታች ሠራተኞች ያላቸው አሰሪዎች የቀጣይነት ሽፋን ለ3 ወራት እንዲያቀርቡ DC ይጠይቃል።

**የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ለስቴት ወይም አካባቢ COBRA ፕሪሚየሞችን ይከፍላል?**

**አዎ።** የፌዴራል መንግስት ለፌዴራል ወይም አካባቢ COBRA ፕሪሚየሞች ይከፍላል። DC የአካባቢ COBRA አለው። የDC COBRA ለ3 ወራት ይቆያል።

**እኔ በ COBRA ውስጥ ከተመዘገብኩኝ፣ የእኔ COBRA ፕሪሚየሞች ለምን ያህል ጊዜ ይከፈላሉ?**

የፌዴራል መንግስት የእርስዎ COBRA ፕሪሚየሞችን ከአፕሪል 1, 2021 እስከ ሴፕቴምበር 30, 2021 ይከፍላል።

**የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ የእኔን COBRA ለ18 ወራት በላይ ያራዝማል?**

**አይ።** የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ COBRAን አያራዝምም። 18 ወራት ለCOBRA መተግበሩን ይቀጥላል። እንዲሁም የDC COBRAን አያራዝምም። ለDC COBRA፣ የ3 ወራት ቆይታ መተግበሩን ይቀጥላል።

**እኔ ከሥራየ ተቀንሼያለሁ። እኔ የፌዴራል መንግስት 100% የCOBRA ፕሪሚየሞቼን እንዲከፍልልኝ ብቁ እሆናለሁ?**

**አዎ።** እርስዎ ከሥራ-ስለተቀነሱ፣ የፌዴራል መንግስት 100% የCOBRA ፕሪሚየሞችዎን እንዲከፍልልዎ ብቁ ይሆናሉ።

**እኔ ከሥራ ስነሳ የትዳር ባለቤቴ እና ልጆቼ በኔ የጤና መድን ስር ተሸፍኗል። የፌዴራል መንግስት 100% የCOBRA ፕሪሚየሞቻቸውንም ይከፍላል?**

**አዎ።** እርስዎ ከሥራ ሲነሱ የቤተሰብዎ አባላት በእርስዎ አሰሪ-ስፖንሰር የሚደረግ ሽፋን ውስጥ ተመዝግበው ከሆነ፣ የፌዴራል መንግስት 100% የCOBRA ፕሪሚየሞቻቸውን ይከፍላል።

**እኔ በአዲሱ ሥራየ በኩል ለሽፋን ብቁ ነኝ። እኔ የፌዴራል መንግስት የCOBRA ፕሪሚየሞቼን በቀድሞ አሰሪየ በኩል እንዲከፍልልኝ ብቁ እሆናለሁ?**

**አይ።** እርስዎ በአሠሪ-ስፖንሰር ለተደረገ ሽፋን ወይም Medicare ብቁ ከሆኑ ብቁ አይሆኑም።

**እኔ ሥራየን ለቅቄያለሁ። እኔ የፌዴራል መንግስት 100% የCOBRA ፕሪሚየሞቼን እንዲከፍልልኝ ብቁ እሆናለሁ?**

**አይ።** ከሥራ-የተቀነሱ ሰዎች ብቻ ናቸው የፌዴራል መንግስት 100% የCOBRA ፕሪሚየሞቻቸውን እንዲከፍልላቸው ብቁ የሚሆኑት። እርስዎ ሥራዎን ስለለቀቁ፣ ብቁ አይሆኑም። እንዲሁም እርስዎ ተገቢ ባልሆነ ስነ-ምግባር ሥራዎን እንዲያቋርጡ ከተደረጉ፣ ብቁ አይሆኑም።

**የፌዴራል መንግስት ለእኔ COBRA ፕሪሚየም ይከፍላል?**

የፌዴራል መንግስት ለእርስዎ መድን ኩባንያ ወይም ለእርስዎ ቡድን ጤና እቅድ በቀጥታ ይከፍላል።

**እኔ ከሥራ ተቀንሼያለሁ እና ሥራየን-መሰረት ያደረገ ሽፋን በዲሴምበር 31, 2020 አበቃ። እኔ ለፌዴራል COBRA ብቁ ነበርኩ ግን አልተመዘገብኩም። ነፃ የCOBRA ሽፋን ለመቀበል አሁንም መመዝገብ እችላለሁ?**

**አዎ።** የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ በፌዴራል COBRA ውስጥ ለመመዝገብ አዲስ እድል ይሰጥዎታል። ከአፕሪል 1, 2021 ጀምሮ፣ ከስራ ሲቀነሱ በመጀመሪያ 60-ቀን የCOBRA ምርጫ ጊዜ ካለፈዎ ወይም ላለመመዝገብ ቢወስኑ እንኳ መመዝገብ ይችላሉ። ከ COBRA ቢወጡም እንደገና መመዝገብ ይችላሉ። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ የ18 ወሩን የፌዴራል COBRA ወይም የ3 ወሩን የDC COBRA አያራዝምም።

እርስዎ ለፌዴራል COBRA ሽፋን ብቁ ከሆኑ የእርስዎ COBRA በጃንዋሪ 1, 2021 ይጀምር እና በጁን 30, 2022 ያበቃ ነበር(18 ወራት ከጃንዋሪ 2021 ጀምሮ)። የአሜሪካ የነፍስ አድን እቅድ ስር፣ ምንም እንኳ መጀመሪያ ባይመዘገቡም አሁንም የ18-ወራት የፌዴራል የCOBRA ሽፋን ውስጥ ስለሆኑ በCOBRA ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ።

**አዲስ መረጃ ሲገኝ የDC Health Link አዲስ ጥያቄዎችን እና ተጨማሪ መረጃን በመጨመር ይህን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን (FAQ) ያሻሽላል።**